# ዘመናዊ ትምህርትና ስለጣኔ - 4

….የቀጠለ

ሁለተኛው የኢትዮጵያ የምሁራን ትውልድ / second generation of Ethiopian intellectuals/ የሚባለው ከጣልያን ወረራ በሁዋላ የተከተለው ሲሆን እነደምናየው ያገር ክህደት ባህል መልኩንና ቅርፁን ቀየሮ የብሄር ብሄረሰቦችን የሙብትና የእኩልነት እውነተኛ /genuine/ የዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን ተላብሶ ይገኛል;;

ለማስታወስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የምሁራን ትውልድ ከሁለተኛው የሚለየው ነጥብ;- የመጀመሪያው ትውልድ የነበራቸው እምነት ለውጥና እድገትና ለማምጣት የሃ/ስላሴን አውቶክራቲክ ስልጣን ተጠቅሞ ዘመናዊ ትምህርትን በማስፋፋት፣ የእድገት እንቅፋት የሆኑትን የስርአቱ የስልጣን ተዋረድ የፊውዳል ሹሞች /traditional elites/ በተማረ ህይል መተካትና ያዲሱን የካፒታሊስት እድገት መፍጠር ራዕያቸው ያድረጉ ሲሆን በተከታዩ ትውልድ ይህ እምነት ተለውጦ የሃ/ስላሴ ለለውጥ ልግምተኝነትና የፊውዳል እሊቱ ማነቆ የለውጥ እድገትን ተብትቦ ማስሩ ብቻ ሳይሆን አገሪቱን ወደ ማህበራዊ ቀውስ ሊከታት እንደሚችል በመገንዘብ ስልጣንን በራሳቸው በተማረው እጅ ለማግባት ና ራሳቸው የለውጥ ሃዋርያ ለመሆን የተነሱ መሆናቸው ነው;;

በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ምሁራን ትውልድ ላይ ያየነው የክህደት ወንጀል ያመጣው አምለኮ-ምዕራብ የአዕምሮ ቅኝ ተገዢነት የአገርን ልዕልና አሳልፎ በመስጠት (የጣሊያን ቅኝ ገዢን በማበር) ሲከሰት ሁለተኛው መልኩን ቀይሮ በብሄር ብሄረቦች የነፃነት ጥያቄ ጀርባ የአገርን ህልውናን በማፍረስና በመፈታተን (የጣሊያን ቅኝ ገዢዎች እጅ) በመሆን ነው;;

የጣሊያን ቅኝ ገዢዎች የኢምፔሪያሊስት ዓላማቸውን እውን ለማድረግ ትልቅ እነቅፋትና ጋሬጣ የሆነባቸውን የኢትዮጵያ አንድነትና ማዕከላዊነት ላይ የነበራቸው የመረረ ጥላቻና ለህዝቧም የነበራቸው ንቀት በቅኝ ተገዢያቸው በኤርትራ አማካኝነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትቀላቀል አብሮ ገብቶ በሁለተኛው የኢትዮጵያ የምሁራን ትውልድ ውስጥም ክህደትን አገር የመገንጠል ወንጀል እነዲከሰት ምክንያት ሆኗል;;

የኢትዮጵያ ምሁራንና የተማሪዎች ንቅናቄ በሁለተኛው ትውልድ ከጥንስሱ ጀምሮ ከኤርትራ ጥያቄ ጋር ቁርኝት ያለው ሲሆን ለተካሄደው ስር ነቀል ለውጥ የራሱን አስተዋፃኦ ከማበርከቱ ጋር የትውልዱንም የትግል አቅጣጫ በመቅረፅ ረገድ ተፅዕኖ እንደነበረው ዶ/ር ሌነጮ ለታ እንዲህ ይገልፀዋል- “ Eritrea incorporation into Ethiopia thus unexpectedly resulted in heightening the grievances of other southern peoples.” /Leenco Leta- The Ethiopian State at the crossroads/

ነገር ግን ከዚሁ ጋር የኤርትራ የነፃነት ጥያቄ አራማጆች ሌላውም ለፍትህና ለዲሞክራሲያዊ ለውጦች የተነሳው ክፍል የሚጋራቸውን ለገዢው መደብና ለነበረው ስርአት ያላቸውን ጥላቻ ብቻ ሳይሆን ያስፋፉት ከጣሊያን ቅኝ ገዢዎች የወረሱትን ፀረ-ኢትዮጵያ አጀንዳና ጭፍን ጥላቻም ጭምር ነው;; የጣሊያን ቅኝ ገዢዎች ለግማሽ ምዕተ ዓመት ኤርትራ ውስጥ ኮትኩተው ያሳደጉት ፀረ ኢትዮጵያ መርዝ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትቀላቀል የጣሊያን ቅኝ ገዢዎች የትሮያን ፈረስ ሆኖ ከውስጥ ያገሪቱን መሰረት ለመቦርቦርም እነዲበቃ አስችሏል;;

ይህም በትግራይና በኦሮሞ ኤሊቶች ጥንፈኛ የአቋምና የትግል መስመር ተንፀባርቋል;; የትግራይ

ኢሊቶች ከኤርትራውያኑ ጋር ያለቸው ቅርብ የዘር ቅርበት፣ የትግራይ ከዘውዱ ጊዜ ጀምሮ መገሸሽ /marginalized/ መደረግና በአማራና በትግራይ ኢሊቶች መሃከል ያለው ስር የሰደደ ባላንጣነት፣ በደቡብ ደግሞ ባለቤት የሆነው /indigenous/ ነዋሪው የገዛ መሬቱን በአማራ ጉልተኞች መነጠቅና የነበረው የገባር የመሬት ስርአት አስከፊ ጭቆና ተደምሮ የትግራይና የኦሮሞ ምሁራንን የኤርትራውያንን ፀረ-ኢትዮጵያ አመለካከት እንዲጋሩና የኤትኒክስ ፖለቲካ እንዲያራምዱ ቅድመ መሰረት የጣለ ሲሆን የትግራይ ኢሊቶች የትግራይን ሙሉ ነፃነት በሁዋላም የአማራን የበላይነት/domination/ ዒላማቸው አድርገው ሲነሱ የተወሰነው የኦሮሞ ኢሊት ክፍል ደግሞ ከዛም አልፎ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ በማነጣጠር ለኢትዮጵያ መፍረስና ለነፃ ኦሮሚያ መመስረት የመገንጠል መንገድን ሊመረጥ በቅቷል;;

እዚህ ላይ የምንረዳው ያለ ኤርትራውያን ጣሊያናዊ ስነ-ልቡና (ኢትዮጵያዊ ለሆነው ነገር በሙሉ ጭፍን ጥላቻና ንቀት በተለይ የአንድነት ጥላ ለሆነው ማዕከላዊ መንግስትነት ጠላትነት ) ያለዚህ ጣልቃ ገብነትና ተዋፅዖ የመገንጠል ጥያቄም ሆነ የኤትኒክስ ፖለቲካ በሁለተኛው ትውልድ ምሁራን ንቅናቄ ስር ለመስደድ እነደማይበቃና እነደማይችል ነው;;

የ "መገንጠል" መርህ ከቅኝ ገዢዎች "ከፋፍለህ ግዛው" መርህ ጋር ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ወይም ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሲሆኑ ዓላማቸውም የቅኝ ገዢዎችን ወይም አገር በቀል ቅኝ ገዢዎችን ማገልገል ነው;;

"ታላቋ ኤርትራ" "ታላቋ ሶማሊያ" "ታላቋ ትግራይ" "ታላቋ ኦሮሚያ" ...ወዘተ የጣሊያን ቅኝ ገዢዎችና የምዕራብ ሚሺነሮች የተባበረ አንድ ህዝብን ፀረ-ቅኝ ትግል /resistance / ለማኮላሸትና ጥላቻን ለመዝራት የተጠቀሙበት መርህ ሲሆን ለአፍቃሬ ፈረንጅ አገር በቀል ቅኝ ገዢዎች ደግሞ አቋራጭና አስተማማኝ የስልጣን መንበር ነው;;

የዛሬዋ "ታላቋ ኤርትራ"ም የዚህ ሃቅ ገሀድ ማረጋገጫ ከመሆኗም በላይ በትናንትናዋ ኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመው ክህደት ምስክርና የትውልዱንም ምሁር በምዕራቡ ዓለም ቅኝ ገዢዎች ላይ የነበረውን ያስተሳሳሰብ ጥገኝነት መግለጫ ቋሚ ማስታወሻ ነች;;

## በአዲሱ ዘመን ዌስትረኒዝምን በኢትዮጵያኒዝም

የዘመናዊ ትምህርትን ዱካ የሚከተለው ምዕራባዊነት ወይም ዌስትረኒዝም አገር አፍራሽ ትውልድ አኮላሽ የአእምሮ ጥገኝነት ያስከተለውና የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት ዘርፈ ብዙ ሲሆን ከሁሉ በፊት ተጠቂውና /victim/ አስተላላፊው የተማረው ክፍል ነው;; እከሌ ተከሌ ፣ ይህ ድርጅት ያ ድርጅት፣ ደጋፊ ተቃዋሚ፣ ያ ትውልድ ይሄ ትውልድ ሳይባል ሁሉም የችግሩ ሰለባ በመሆኑ ያለ ምንም የሃሳብ ቱማታ /illusion/ ጥርት ያለ ግልፅ ግንዛቤ ማግኘትና አልፎም የሁሉም በግልና በጋራ ንስሀና ሱባዔ መግባት የችግሩ መቀረፊያ የመጀመሪያ ደረጃ ነው;; ያለንበትም ወቅትም ሆነ የታሪካችን የእድገት ደረጃና ከፊታችን ያለው መስቀለኛ መንገድ ግድ የሚለው ሃቅ ይህ ሆኖ ይገኛል;;

ለዘለቄታዊ ሰላም አንድነትና እድገት የጋራ መድሃኒት በጋራ መሻት ህዝባዊ ትውልዳዊና ህሊናዊ ግዴታ ይሆናል;; መንገዱም የፈረንጅ ጭምብላችንን አውቀንና አውልቀን ወደ ስረ-መሰረታችን መመለስና ኢትዮጵያውነትና ኢትዮጵያኒዝምን ማጠናከር ነው;; በርግጥም የፈረንጅ ጭምብላችንን

ስናወልቅ የተጠናወተን ራሳችንን ‘ፍፁም’ና ‘ሁሉን አዋቂ’ አድርጎ ማየቱ አብሮ ይወልቃል.... የእኔ መንገድ ብቻ ትክክል ነው... እኔ ካልኩት በቀር ይሰባበር ...ወዘተ ቀኖናዎች ተወግደው ሁላችንም እኩል ኢትዮጵያዊ መሆናችን ይገለጥልናል;; ማንም ሰይጣን ማንም መልአከ እንደልሆነና የእውነት ሞኖፖሊ እነደሌለ እንረዳለን;; ልቦናችንን የጋረደው ለሁሉም በሁሉም ፈረንጃዊ ጭፍን ጥላቻ ሲሟሸሽ በቦታው በጎ ፈቃድ፣ ገንቢ ሃሳብ፣ መተማመን፣ መተጋገዝና ወንድማማችነት ይተካሉ;; ፀረኛነትና የጥፋ አጥፋው ተፃራሪነት በገንቢ ተቃዋሚነትና የህግ የበላይነት ይተካል;;

ለዚህም ውስጣችንን ፊት ለፊት ለማየትና ንስሀ ለመግባት በግልፅና በድፍረት መነሻ ግዜው አሁን ነው;; ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት አንድ የውጭ ጋዜጠኛ ላቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ እነዲህ ብለው ነበር;; “Of course everybody's thinking evolves over time. Only dead people cease learning, and I am not certified dead yet. So I am still learning. Over the years I've come to recognize that democratization in Ethiopia is not just a matter of choice. It's a matter of national survival. I am deeply convinced that we either democratize and have a good chance of surviving, or if we fail to do so, we disintegrate. That is a significant evolution in my thinking. I know more now than I did in the past about the process of democratization. I know more about the pitfalls…” ይህ መልካም ጅምርና አርአያ ከሁሉም የሚጠበቅና ልንከተለው የሚገባ መንገድ ነው;; እርቅ ከራሳችን ጋር ስንጀምር ነው ከውጭውም ጋር የምናርቀው;; ኢትዮጵያኒዝምንም ማራመድ የሚቻለው እረቅና ሰላም ሲውረድ ነው ;;

የኢትዮጵያኒዝም መነሻ ነጥቡም ሀ ሁ መቁጠር ወደ ጀመርንበት የገጠርና የከተማ ት/ቤቶች ቅጥር ግቢ ተመልሰን፣ ወደ ገበሬው ቀዬና ማሳ አቅንተን፣ የከተማውንም ጎዳና ወጥተን ወርደንበት በኢትዮጵያዊነት ህይወት በአዲስ ሰለጥነን በማሰልጠን ነው;; በዚህ መንገድ ነው ማንነታችን መመለስና ወደ ማንነታችን መመለስ የምንችለው;;

የምዕራባዊው ዓለም ርዕዮት (Eurocentric view) ተሸካሚ የሆነው ዘመናዊ ትምህርትና ምሽጉ የዘመናዊ ትምህርት ተቋም በኢትዮጵያኒዝም (Ethnocentric view) ፖሊሲ እነደገና መቀረፅ ያለምንም ጥርጥር የእድገት የማዕዘን ድንጋይ ነው;; አገራችንንም እኛንም ለሰለባነት /victim/ ያበቃንን ዘመናዊ ትምህርት ህይወትና እስትንፋስ ሰጥተነው ከዌስተርኒዝም ተላቅቆ ኢትዮጵያኒዝምን ማገለገል የሚችለውና ከድህነትና ከረሃብ የምንላቀቅበት ብቸኛው መንገድ በዚህ መልክ ነው;; ካፒታሊዝም ሶሻሊዝም ኤትኒስዝም ...የፈለገው አይነት -ኢዝም ፍሬ ሊያፈራ የሚችለው መሰረቱን ኢትዮጵያኒዝም ላይ ሲያደርግ ብቻ ነው;;

**ኢትዮጵያኒዝም ማለት ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በጥቅሉና የእያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ በተናጥል የኑሮ ስልት /Mode of life/ ማለት ነው;;**

**ኢትዮጵያኒዝም ማለት የሰማንያ ሶስቱም ብሄር ብሄረሰብ ባህል፤- ቋንቋ ወግ ልምድና ስርአት ማለት ነው;;**

**ኢትዮጵያኒዝም ማለት ለዘመናት የቆየውና ዛሬ የእኛ ትውልድ የተረከበው ታላቅ እሴት -አብሮ የመኖርና የመቻቻል በጎ ባህል፣ የአንድነት ሞራልና ስሜት ማለት ነው;;**

***ኢትዮጵያኒዝም ማለት በጦርነት አውድማው የአድዋ ፤ የካራማራ የባደም መንፈስ … በሰላሙም መድረክ የነሃይሌ ገ/ስላሴ የ "ይቻላል" ወኔ…. በነገውም የኤኮኖሚ ተአምር /miracle/ ያለን ፍፁም እምነት ማለት ነው;;***

***ኢትዮጵያኒዝም ማለት አዲስ በምንጀምረው ሁለተኛው ሺህ ዓመት በአዲስ እውቀት፣ በአዲስ ራዕይና በአዲስ ተስፋ የምንሰባሰብበት ጥላ ማለት ነው;;***

***ኢትዮጵያኒዝም ማለት በራስ መተማመንና በፈረንጅ ምትክ የመንደራችንና የቀያችን አድባርና አውጋር ማምለክ ማለት ነው;;***

"….We must come up with a new definition of development and modern education . Instead of defining modernization as the process by which we detach our thought and will from our roots and traditions so as become civilized like westerners, we must redirect it toward the task of developing Ethiopianism. Technological and scientific advances of the west will serve as inspiration in the sacred of bringing to reality the potentials of our legacy.

And the best way to revise modern education is through the revival of the tradition that enabled Ethiopia to survive and preserve its independence for so long. We will get out of dependent thinking when we center ourselves in such a way that the West descends from the status of a model to that of particular experience from which we can learn many things without however being decentered and losing our perspective. The revival of tradition is how we center ourselves so as to develop a purely pragmatic relation with the West instead of endorsing its alleged normativeness." **በማለት ዶ/ር መሳይ ከበደ ከላይ በሰፊው የተዘረዘሩትን የዘመናዊ ትምህርት ድክመቶችና የስርአተ ፖሊሲውንም የለውጥ አቅጣጫ ጭብጥ ሃሳብ በሚቋጭ መልክ ይገልፀዋል;;**

**እኔም ከመጪው ሁለተኛው ሺ ዓመት መግቢያ ጋር አገራችን ኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የምትገለጥበት፣ ድህነትና ረሃብን፣ መከፋፈልንና እርስ በርስ መናቆርን ወደ ሁዋላ ጥላ፣ በአዲሱ ዓመት፣ በአዲሱ ሺህ ዘመን መግቢያ *"የሰላም የአንድነት የኢትዮጵያ ሰልጣኔ ምንቻት ግባ የምዕተ ዓመት ችግር የሆነው እጅ አዙር ቅኝ ተገዥነትና ውጤቱ ድህነትና ጦርነት ውጣ !"*የምንልበት እንዲሆን እየተመኘሁ ከአክብሮት ጋር መጣጥፌን እዚሁ ላይ እቀረቅባለሁ;;**

**ኢትዮጵያ በግዜሩ ድጋፍ፣ በልጆቿ አስተዋይነትና አንድነት ከችግሯ በላይ ትቆማለች!**

**ጃዊሳ** (bekulu05@Yahoo.com)

**ጥቁር የነበረ - ኮፊ በተፈጥሮው፣**
**ድንገት ተጠግቶ - ያ ወተት ሲውጠው**
**ከቶ ለምን ይሆን - ነጬን የሚሆነው።**
**ገሞራው**